# የኢህአዴግ የሴቶች ሊግ ፕሮግራም

[የፀደቀ]

ግንቦት 2001 ዓ.ም

# የኢህአዴግ የሴቶች ሊግ ረቂቅ ፕሮግራም

I. መግቢያ:-

የአገራችን ሴቶች ለዘመናት ስር ሰዶ በቆየው ድርብ ጭቆና ለከፍተኛ ስቃይ በመዳረጋቸው በአንድ በኩል እንደማንኛውም ጭቁን የህብረተሰብ ክፍል የሚደርስባቸውን ጭቆናና በደል ሲታገሉ በሌላ በኩል ደግሞ በሴትነታቸው ብቻ ተነጥሎ ይፈፀምባቸው የነበረውን በደል ለመርታት ጣምራ ትግል አካሂደዋል፡፡ እድሜ ልካቸውን በጭቆናና በስቃይ እንዲኖሩ የፈረደባቸውን አፋኝ ስርአትና የአምባገነኖችን እድሜ ለማሳጠር  ወሳኝ በሆነው የትጥቅ ትግል ከተራ ተዋጊነት እስከ አመራርነት በመሳተፍ የድሉ ብቻ ሳይሆን የታላቁ መስዋእት ተጋሪዎች ከመሆናቸውም በላይ ከከተማ እስከገጠር ሴቶች ያልተሳተፉበት የትግል መስክ፣ ያልከፈሉት መስዋእትና አሻራቸውን ያላሳረፉበት የድል መድረክ የለም፡፡

የአገራችን ሴቶች በከፈሉት ከባድ መስዋእት ጭምር አዲስ ጐህ  ከፈነጠቀ ካለፉት አመታት ወዲህም ድህነትንና ኋላቀርነትን ለማስወገድ በሚካሄደው ትግል ሴቶች ከወንድሞቻቸው ጐን ተሰልፈው ተፋልመዋል፡፡ በገጠርም በከተማም ዴሞክራሲያችን ስር እንዲሰድ፣ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን፣ ልማት እንዲስፋፋና የህዝብ ተጠቃሚነት እንዲዳብር በዚህ ሁሉ ድል ውስጥ ደግሞ የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዲያድግ በፅናት ተረባርበዋል፡፡ አገራችን ባለፉት አመታት ለተጐናፀፈችው ዙሪያ መለስ ድል ሴቶች የበኩላቸውን አስተዋፅኦ በከፍተኛ የሃላፊነት መንፈስ አበርክተዋል፡፡

በመላው የአገራችን ህዝቦች ርብርብና በራሳቸው በሴቶች ተሳትፎ ጭምር  በመካሄድ ላይ ካለው አገራዊ ለውጥ ሴቶች በብዙ መስኮች ተጠቃሚ መሆን ጀምረዋል፡፡ ለዘመናት ስር ሰደው የቆዩ የፖለቲካዊና የህግ ስሪቶችን ለማፍረስ ወሳኝ ሚና በሚጫወተው ህገ መንግስታችን የሴቶች የእኩልነት መብቶች እውቅናና ጥበቃ ተደርጐላቸዋል፡፡ በሴቶች ላይ ከፍተኛ በደል ያደርስ የነበረው የቀድሞ ቤተሰብ ህግ በአዲስ የቤተሰብ ህግ እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡ ሴቶች የመማርና የመስራት ሰፊ እድል ተከፍቶላቸው በዚሁ እድል በከፍተኛ ደረጃ በመጠቀም ላይ ይገኛሉ፡፡

የአገራችን ሴቶች በተናጠልና በጋራ ባካሄዱት ትግል ያስመዘገቧቸው ድሎች ሰፊና መሰረታዊ ቢሆኑም ዘመናትን ያስቆጠረው ኃላቀርነትና የድህነት ችግር እንዲህ በአጭር ጊዜ ነቃቅሎ መጣል ይቻላል ተብሎ አይገመትም፡፡ በመሆኑም ዛሬም ቀላል የማይባሉ ኃላቀርነት  አዝማሚያዎችና ተግባራት እንደተንሰራፉ ይገኛሉ፡፡ የኢትዮጵያ ሴቶች እውነተኛ ማህበራዊ ነፃነት ተረጋግጧል ማለት የሚቻለው የተጀመረው ትግል ተጠናክሮ በድህነትና በኋላ ቀርነት  ላይ የተጀመረው ዘመቻ የተሟላ ድል ሲያገኝ ብቻ ነው፡፡ ይህ ድል ሊገኝ የሚችለው መላው ፀረ ድህነትና ኋላቀርነት ትግላችን በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ድርጅት እየተመራ ሲታገልና የሴቶችም ጥያቄ በዚሁ ማእቀፍ ሲመራ ነው፡፡የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አላማዎች እና ፖሊሲዎች የተፈለገውን ያህል ውጤት እንዲያመጡና እንዲሳኩ ሴቶች ያላቸዉን ብቃትና ስነምግባር አዳብረዉ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ

ይጠበቅባቸዋል። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ራሳቸዉን ከጎጂ ልማዳዊ አሠራር አላቀዉ ለሴቶች እኩልነት በፅናት በመታገል በህገ መንግስቱ የተደነገገላቸዉን በኢኮኖሚያዊ፣ በፖለቲካዊና በማህበራዊ ጉዳዮች ከወንዶች ጋር እኩል የመሳተፍ ሚናቸዉን ተጫዉተዉ ከዉጤቱም እኩል ተጠቃሚ ለመሆን የኢህአዴግን አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አመራር የተቀበሉ ሴቶች በራሳቸው አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ የፆታ አደረጃጀት ተሰባስበው በመላው የአገራችን ህዝቦች ትግልና በራሳቸው ጥያቄ ዙሪያ ተገቢ ሚናቸውን ለመጫወት ይችሉ ዘንድ የኢህአዴግ የሴቶች ሊግ የሚመራበት ፕሮግራም እንደሚከተለዉ ተቀርጿል።

II. የኢህአዴግ ሴቶች ሊግ የሚመራባቸው መርሆዎችና መነሻዎች፣

1. የኢትዮጵያ ሴቶች ለዘመናት በድርብ ጭቆና ስር እንዲማቅቁ ያደረጋቸው ፀረ ዴሞክራሲያዊው አገዛዝ የአገራችንን እድገትና ግስጋሴ ገትቶ መላውን ህብረተሰብ ለስቃይና ለእንግልት ዳርጐት የቆየ መሆኑን በመገንዘብ፣
2. አምባገነናዊው አገዛዝ በመላው የአገራችን ጭቁን ህዝቦች ላይ ያካሄደው አስከፊ ብሄራዊና መደባዊ ጭቆና በሴቶች ላይ ሰፍኖ ለቆየው የወንድ የበላይነትና የፆታ ጭቆና መሰረታዊ ምንጭ እንደነበርና ይህ ስርአት ሴቶችን ጨምሮ በመላው ህዝባችን ትግል ሲገረሰስ ለነፃነትና ዴሞክራሲ፣ ለእድገትና ብልፅግና፣ ለእኩልትና ለፍትህ መስፈን የተመቸ አገራዊ ሁኔታ መፈጠሩን በመገንዘብ፣
3. የአገራችን ሴቶች በህገ መንግስት በተደነገጉ መሰረታዊ መብቶች በታሪካቸው ለመጀመሪያ ጊዜ እኩልነታቸው ህጋዊ እውቅና ማግኘቱ ሴቶች የተጐናፀፍነው ከፍተኛ ድል መሆኑን በመቀበልና ይህን ድል ለመጠበቅና ለማስፋት በሚካሄደው የመላው ህዝብ ትግል ሴቶች እንደተለመደው በፅናትና በቁርጠኝነት አስተዋፆዋችንን ማበርከት እንዳለብን በማመን፣
4. ህገ መንግስታችንን መሰረት በማድረግና በሴቶች ላይ የሚደርሱ በደሎችን ለማስወገድ የሚያግዙ ተጨማሪ የህግ ማእቀፎች ተዘጋጅተው በተለይ የቤተሰብ ህግ ወጥቶ በተግባር ላይ መዋል መጀመሩ ለዘመናት የቆየውን አድሎ ለመታገል የተመቸ ሁኔታ እንደፈጠረ በመቀበል፣
5. ሴቶች ባለፉት አመታት በሁሉም መስኮች በርካታ ድሎችን እንደተጐናፀፉ የሚታመን ቢሆንም ስር የሰደደው የወንድ የላይነትና የትምክህት አስተሳሰብና ተግባር በአጭር ጊዜ ሙሉ በሙሉ ሊወገድ የሚችል እንዳልሆነ በመገንዘብ ዛሬም ህጋዊ፣ ተቋማዊና ልማዳዊ በሆኑ ጉዳዮች እንዲሁም በለት ተለት የህብረተሰብ ተግባርና እኩል ለመወዳደር በማያስችለው ነባራዊ መነሻ ምክንያት በሴቶች ላይ የሚደርሰውን በደል የመታገልን አስፈላጊነት በማመን፣
6. መንግስት ይህን በመገንዘብ የሴቶችን እኩልነት ለማረጋገጥ በተለይ ደግሞ ሴቶች እኩል እድል እንዲሰጣቸው ለማድረግ የወሰዳቸውን መሰረታዊና አበረታች ርምጃዎች በማድነቅ፣ ይህም ሆኖ

መንግስት ለሴቶች እኩልነት መከበር ከሰጠው መሰረታዊ አመራርና ድጋፍ ባሻገር ዛሬም መፍትሄ የሚሹ በርካታ መሰረታዊ ችግሮች እንደተከማመሩ የሚገኙ መሆናቸውን በመገንዘብ፣

7. መንግስት ለሴቶች እኩልነት የተሰጠው ትኩረት ይበልጥ መጠናከር እንዳለበት ወስኖ ይህን በትክክለኛ አቅጣጫ ለማስፈፀም እንዲቻል የሴቶችን ትግል ለመምራት የሚያስችል የትግልና የለውጥ - ኬጅ አዘጋጅቶ በሴቶች ባለቤትነትና ተሳትፎ ተግባር ላይ ለማዋል ያደረገው ርብርብ ትክክለኛና የተቀደሰ ተግባር እንደሆነ በመቀበል፣
8. የአገራችን ሴቶች የእስካሁኑ ትግላቸው ለድል ያበቃቸው በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ድርጅት በመመራትና በዚህም ውስጥ የሴቶችን የተደራጀ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ በማረጋገጥ እንደሆነ በመቀበል፣
9. ድህነትንና ኋላቀርነትን እንዲሁም የዚህ ተቀጥላ የሆነውን የፆታ ጭቆና ለማስወገድ የአገራችን ሴቶች ከወንድ ወንድሞቻቸው ጋር ጠንካራ የትግል አጋርነት ፈጥረው ሊረባረቡ እንደሚገባ በመቀበል፣
10. ሴቶች ለማህበራዊ ፍትህና ለእኩልነት የሚያካሂዱት ትግል ግቡን የሚመታው በአንድ በኩል በሴቶች ጥያቄ ላይ የተመሰረተ የኪራይ ሰብሳቢነት አዝማሚያ በትግል ሲወገድና ሴቶች በልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ሲመሩ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሴቶች በየአካባቢያቸው አሳሳቢ ሆነው በሚያገኙዋቸው ጥያቄዎች ዙሪያ የትግል ማህበራት ፈጥረው መብታቸውንና ጥቅማቸውን ሲያስከብሩና ሲያሰፉ እንደሆነ በመቀበል፣
11. ሊጉ የሴቶችን ትግል ወደፊት ለማራመድ የሚፈጠሩ ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች ጠቃሚና አስፈላጊ ቢሆኑም በተበተነ መንገድ እስከሄዱ ድረስ ትግሉን በአጭር ጊዜ ውጤታማ ለማድረግ እንደማይችሉ በመገንዘብ አገራዊ የሴቶች ፌዴሬሽን ሲቋቋም በመደገፍ፣
12. የኢህአዴግ ሴቶች ሊግ በኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመርና ድርጅታዊ አመራር እየተመራ ለሚከተሉት ተጨማሪ ጉዳዮች ይታገላል፡፡

## III. የኢህአዴግ የሴቶች ሊግ የፖለቲካ መርሃ ግብር

### የኢህአዴግ የሴቶች ሊግ የፖለቲካ ዓላማ

ሴቶች ህገ መንግስቱ ያረጋገጠላቸውን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች በተገቢው በመገንዘብ እነዚህም መብቶች በተሟላ ሁኔታ እንዲከበሩላቸውና፣ በአገሪቱ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የነቃ ነፃና ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ በማድረግ ዴሞክራሲያችን ስር እንዲሰድ፣ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ብሎም በእኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ የኢትዮጵያ ህዝቦች ጠንካራ አንድነት እንዲጎለብትና በሂደቱም ዘላቂ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይህን ስትራቴጂያዊ የፖለቲካ ዓላማ ለማሳካትም የሚከተለውን የፖለቲካ መርሃ ግብር ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

1. ህገ መንግስታዊ ዋስትና ባገኙት የዲሞክራሲ መብቶች ሴቶች ዋነኛ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ

1.1. በህገ መንግስቱ ዕውን የሆኑት ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለሴቶች ብሎም ለሁሉም ዜጎች በተሟሏ አኳኋን እንዲከበሩና ይበልጥ እየዳበሩ እንዲሄዱ መታገል።

1.2. የሁሉም ዜጎች መብቶች በሚከበርበት የዴሞክራሲ ስርዓት ውስጥ ሴቶች በነዚህ መብቶች በሰፊውና በተደራጀ አኳኋን እንዲጠቀሙ መታገል።

1.3. ሴቶች ህገ መንግስቱ ያረጋገጠላቸውን ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲጠበቁላቸውና በስራ እንዲተረጎሙ በፅናት መታገል።

1.4. ለዲሞክራሲ ማበብ ተፈላጊ ከሆኑ አደረጃጀቶች ውስጥ አንዱ የብዙሃን ማህበራት አደረጃጀት በመሆኑ እነዚህ የብዙሃኗ ሴት አደረጃጀቶች ነፃነታቸወ ተጠብቆ ለአባላት መብት መከበር በፅናት እንዲቆሙና ህጉን ተከትለው እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ መታገል።

1.5. እነዚህን መብቶች ለማፈን፣ ለመሸራረፍ፣ የዴሞክራሲ ስርዓቱን ለመናድና ለመቀየር የሚደረግን ማንኛውም ህገ ወጥ ተግባር በፅናት መታገል።

2. እየተገነባ ባለው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሰፊዋን ሴት ነፃ፣ ዲሞክራሲያዊና የተደራጀ ተሳትፎ ማረጋገጥ

2.1. የሴቶች ችግሮች ውስብስብና ዘርፈ ብዙ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በመንግስትና በህብረተሰቡ በኩል ለችግሮቻቸውና ለመፍትሄዎቻቸው ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኙ መታገል።

2.2. ሴቶች ነፃና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ሃሳባችውን የሚገልፁበት በእቅድ ዝግጅትና አፈፃፀም ረገድም የሚሳተፉባቸው መድረኮች እንዲፈጠሩና በተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎችም በተገቢው እንዲጠቀሙ መስራት።

2.3. ሴቶች በአጠቃላይ በህብረተሰቡ ጉዳዮች በተለይም ደግሞ በራሳቸው ጉዳይ በሰፊውና በተደራጀ አኳኋን ለማሳተፍ የሚያስችል ስርዓት እንዲፈጠርና እንዲጠናከር መታገል።

2.4. ሴቶች በርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጥያቄዎች ያሏቸው በመሆኑ በራሳቸው ጉዳይ ቅድሚያ ተቆርቋሪ፣ ተጎጂና ተጠቃሚ መሆናቸውን በመረዳት ችግሮቻቸውን ለመለየትም ሆነ መፍትሄ ለማፈላለግ ማዕከል መሆናቸውን መረዳትና ማመን ለዚህም በስፋትና ተከታታይነት ባለው ሁኔታ መድረኮች እንዲመቻቹ መታገል።

2.5. ሴቶች ዋነኛ ችግር ፈቺ ሃይል መሆናቸዉን እንዳይገነዘቡ የሚያደርጓቸውን አዝማሚያዎች በቀጣይነት በመታገል የማስተካከልና በራስ የመተማመን አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ የተጠናከረ ስራ መስራት።

2.6. ሴቶችን ዝቅ አድርገው የሚመለከቱና የፆታ የበላይነትን የሚያንፀባርቁ የትምክህት አስተሳሰቦችና ተግባራትን እንዲሁም በሴቶች ላይ የሚደርሰን በደል በዲሞክራሲያዊ አኳኋን በፅናት መታገል።

2.7. ሴቶች ባገኙት መድረክ በብቃት እንዳይጠቀሙና ለዚህ እንቅፋት የሆኑትን ዝንባሌዎችን እየለዩ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ በሴቶች ግንባር ቀደም ተሳትፎ እንዲፈታ መታገል።

2.8. ሴቶች በፍላጎቶቻቸው ዙሪያ እንዲደራጁና ለሴቶች የጋራ ጥቄዎች የጋራ አደረጃጀቶች እንዲጎለብቱ ማድረግ እና ሴቶች በነዚህ አደረጃጀቶች አማካይነት መብትና ጥቅማቸውን እንዲያስከብሩ፤ ዴሞክራሲያዊ አሰራራቸው የተጠበቀ እንዲሆን መታገል::

2.9. የተለያዩ የሴቶች አደረጃጀቶች የሴቶችን ትግል በላቀ ደረጃ ወደ ፊት ለማራመድ እንዲያስችል አገራዊ የሴቶች ፌደሬሽን በመደራጀት አደረጃጀቶቹም በዲሞክራሲያዊና በዕኩልነት ላይ የተመሰረቱ እንዲሆኑ መታገል::

2.10. በህገ መንግስቱ በቤተሰብ ህጉና በሌሎች ህጎች የተከበሩላቸው መብቶች በተገቢውና በቀለጠፈ መንገድ ተግባራዊ እንዲሆኑና የህግ ጥበቃ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲጠናከር መታገል::

2.11 የስርዓተ ፆታ እኩልነት እንዲረጋገጥና ፆታዊ ክፍተትን ለማጥበብ ሴቶች በትምህርት በአመራርና ዉሳኔ ሰጭነት የሚኖራቸዉ ተሳትፎ እንዲጠናከር መታገል::

2.12. ሴቶች በአመራርና ውሳኔ ሰጭነት የሚኖራቸው ተሳትፎ እንዲጠናከርና እንዲያድግ መታገል::

3. ሴቶች በህዝቦች መብት መከበር፣ በእኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ያላት አገር ለመገንባት የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ ማስቻል::

3.1. በህገ መንግስቱ የተረጋገጠው የብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል ያላቸው መብት እንዳይሸራረፍ በፅናት መታገል::

3.2. ህዝቦች ህገ መንግስታዊ መብታቸው በተከበረበት ሁኔታ በነፃ ፍላጎታቸውና በመፈቃድ ላይ የተመሰረተ አንድነት እንዲኖራቸው በትጋት መታገል::

3.3. ሴቶች የሁሉም ብሄሮችና፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ታሪክ እንዲታወቅ፣ባህላቸው እንዲጎለብትና እንዲከበር የበኩላቸውን መስራት

3.4. የህዝቦችን ዴሞክራሲያዊ አንድነት የሚሸረሽሩ የጠባብነትና የትምክህት አመለካከቶችን አምርሮ መታገል::

3.5 በየደረጃው የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ጉድለቶች እንዲስተካከሉ መታገል::

3-6 የክራይ ሰብሳቢነትንና ብልሹ አሠራሮችን እንዲሁም አመለካከትና ድርጊት በግንባር ቀደም በፅናት በመታገል የብዙሀኗን ሴት የልማት ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ::

## IV የኢኮኖሚ መርሃ ግብር

## የኢህአዴግ የሴቶች ሊግ የኢኮኖሚ አላማ

በአገራችን ህዝብን በየደረጃው ተጠቃሚ የሚያደርግ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው፣ የኢኮኖሚ ልማት ለማረጋገጥ በተቀየሰው የልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ሴቶች በብቃት እንዲሳተፉና እንዲጠቀሙ ማድረግ፡፡

1. ገጠርንና ግብርናን ማዕከል ባደረገው የልማት ስትራቴጂ ውስጥ የሴቶችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፡፡

1.1. የእማወራ ሴቶች የመሬት ተጠቃሚነት መብት በተሟላ ሁኔታ እንዲከበርና የይዞታ ማረጋገጫ ተጠቃሚ እንዲሆኑና ያለ አግባብ እንዳይነጠቁ መታገል፡፡

1.2. እንደሃገር ያሉንን ሃብቶች መሬትና የሰው ጉልበት በላቀ ደረጃ ለመጠቀም እንዲያስችል በየቀበሌው ሊታረሱ የሚችሉና በግል ያልተያዙ የእርሻ መሬቶች በፍትሃዊ መንገድ ለሴቶች እንዲከፋፈሉ መስራት፡፡

1.3. የሚወጡ የግብርና ልማት ዕቅዶች፣ ፕሮግራሞች፣ የኤክስቴንሽን - ኬጆች በሙሉ ሴቶችን በተገቢው የሚያሳትፉ እንዲሆኑ መታገል፡፡

1.4. የሴቶች የብድር አገልግሎት ተጠቃሚነት በበለጠ እንዳይረጋገጥ የሚያደርጉ የአመለካከትና የአፈፃፀም ማነቆዎችን በመታገል፣ የብድር አገልግሎቱን በተገቢውና በበቂ ሁኔታ እንዲጠቀሙና የቁጠባ ባህል እንዲያዳብሩ መስራት፡፡

1.5. ሴቶች በህብረት ስራ ማህበራት በስፋት እንዲደራጁና ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ መስራት ፡፡

1.6. ሴቶች ለምርቶቻቸው የተሻለ ገበያ ማግኘት የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር መስራት፡፡

1.7. ሴቶች ከግብርና ውጭ በሆኑ የስራ መስኮች በተደራጀ አኳኋን በመሰማራት ገቢያቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ፡፡

1-8 አርብቶ አደሯ ሴት የእንስሳት ሀብትን በአይነትና በመጠን በማሻሻል በቂ የእንስሳትና የእንስሳት ተዋፅኦ ለገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ እንድትሆን የተቀናጀ ተልማት ስራ ማካሄድ፡፡

1-9 ሴቶች ከጠባቂነትና ከተረጂነት አመለካከት ተላቀው በራሳቸው ጥረት ችግሮችን ለመፍታት እንዲችሉ መታገል፡፡

## 2. በከተማና ኢንዳስትሪ ልማት ስትራቴጂ ውስጥ የሴቶችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

2.1 በከተማ የሚገኙ ሴቶች በከተሞች በሚካሄደው ልማት ንቁ ተዋናይና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ።

2.2 በከተማ የሚገኙ ስራ አጥ ሴቶች በየደረጃው ከሚገኙበት ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር በመለየት የልማትና የለውጥ - ኬጅ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደራጅተው ችግሮቻቸውን የሚፈቱበት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ማድረግ።

2.3 ሴቶች በከተሞች በሚካሄዱ ልዩ ልዩ የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማ
ት የማቋቋምና የማስፋፋት ስራዎች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ መስራት።

2.4 በከተማ የሚገኙ ሴቶች የብድር አገልግሎት በበቂ ሁኔታ እንዳያገኙ የሚያግዷቸውን አሰራሮች በመለየት እንዲፈቱ መታገል።

2.5 በከተማ የሚኖሩ ሴቶች በየትኛውም ቦታና ጊዜ የራሳቸውን ንብረት የማፍራት በንብረቱም የመጠቀም መብታቸው እንዲጠበቅ መታገል።

2.6. በመንግስት መስሪያ ቤትም ሆነ በግል ተቋማት ተቀጥረው የሚሰሩ ሴቶች በህግ የተደነገገ መብቶቻቸዉና ጥቅሞቻቸዉ እንዲከበር መታገል።

2.7. በንግድና ኢንቨስትመንት ስራ ላይ የተሰማሩ ሴቶች ኢኮኖሚያቸውን ለማሳደግ በሚያደርጉት ጉዞ በሴትነታቸው ምክንያት የሚያጋጥሟቸው ችግሮች ሲኖሩ የሚፈቱበት አግባብ ላይ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠርና ጥረታቸውን ማበረታታት።

2.8. ሴቶች በከተማ ግብርና ላይ ላቅ ያለ ሚና እንዲኖራቸው ማበረታታት።

2.9. በከተማ የሚገኙ ሴቶች ገቢያቸውን ለማሳደግ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ውጤታማ የሆነ የምርትና የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ማድረግ።

## V. ማህበራዊ መርሃ ግብር

## የኢህአዴግ የሴቶች ሊግ ማህበራዊ አላማ

በየደረጃው የተሟላ ማህበራዊ ለውጥ እንዲመጣ የሴቶችን ማህበራዊ ችግሮች ለመፍታት በሚያስችሉት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አተገባባር ላይ ሴቶች ዋነኛ ሃይልና ንቁ ተሳታፊ በመሆን ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል።

## 1. ትምህርት

1.1. ሴቶች በላቀ የትምህርትና የስልጠና እድል እንዲበቁ መስራት ።

1.2. በትምህርት ገበታ ላይ ህፃናትና ወጣት ሴቶች ጥራቱ የተጠበቀ ትምህርት እንዲያገኙና ትምህርትን በማስፋፋት ሂደት የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ በሚካሄደው ጥረት ላይ ሴቶች ንቁ ተዋናዮች እንዲሆኑ በትምህርት ጥራትና በትምህርት ተቋማት ማሻሻያ ፕሮግራም ውስጥ የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ።

1.3. በየደረጃው ያለው የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ ከወንዶች የትምህርት ተሳትፎ እኩል እንዲሆን መስራት፡፡

1.4. ተማሪዎች በስነ ምግባርና ስነ ዜጋ እሴቶች ትምህርት እንዲታነፁ የበኩላቸውን ጥረት ማድረግና ትምህርት ቤቶች የሴቶች እኩልነትና መብት የተከበረባቸው እንዲሆኑ ጥረት ማድረግ ፡፡

1.5. ሴት ልጆችን የማስተማር አስፈላጊነት ላይ ያሉ የግንዛቤ ጉድለቶች፣ የአስተሳሰብ ችግሮች እንዲቀረፉ መስራት፡፡

1.6. ያልተማሩ ሴቶች ከመሰረተ ትምህርት ጎን ለጎን እንዲሁም በልዩ ልዩ ምክንያቶች ትምህርታቸውን ያቋረጡ ሴቶች ፍላጎታቸውን መሰረት ያደረገ የሙያ/ክህሎት ስልጠና እንዲያገኙ መስራት፡፡

1.7. በችግር ምክንያት ትምህርታቸውን ያቋረጡ ሴቶች ትምህርታቸውን የሚቀጥሉበት አስፈላጊው ሁኔታ እንዲመቻች ጥረት ማድረግ፡፡

1.8. ሴት ተማሪዎችን ከትምህርት ገበታቸው የሚነጥሉ የሃይል ጥቃቶች፣ የፆታ ትንኮሳዎችን ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ በተደራጀ አኳኋን መታገል፡፡

1.9. የቤት ውስጥ የስራ ጫናን የሚያቃልሉ ቴክኖሎጂዎች እንዲስፋፉ መስራትና ሴት ተማሪዎች የተሻለ የጥናት ጊዜ እንዲኖራቸው መታገል፡፡

1-10 በከፍተኛ ተቋማት ዉስጥ የሚገቡ ተማሪዎች ዉጤታማ ለማድረግ ልዩ ድጋፍ እንዲያገኙና በፆታ ምክንያት የሚደርስባቸዉን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለማስወገድ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር መስራት፡፡

1-11 በቴክኒክና ሙያ የሴቶችን ተሣትፎ በማሣደግ በሙያ ተክነዉ ኢኮኖሚያቸዉ እንዲያሣድጉ መታገል፡፡

## 2. ጤና

2.1 ሴቶች በሽታን የመከላከል ግንዛቤያቸውን በማሳደግ ለበሽታ ያላቸውን ተጋላጭነት መቀነስ፣ በመከላከልና በመሰረተ ጤና ላይ ያተኮረ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማስቻል፣ በተለይም የግል ንፅህናና የአካባቢ ንፅህናን የመጠበቅ እንዲሁም የአመጋገብ ስርአትን በማስተካከል ዙሪያ የባህል ለውጥ ማምጣት፡፡

2.2 ሴቶች ኤች አይቪ ኤድስና ሌሎች ተዛማጅ በሽታዎች የሚተላለፉበትን የሚስፋፉበትን እንዲሁም መከላከያ መንገዶችን እንዲገነዘቡ በማድረግ የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲያመጡ መስራት፡፡

2.3. የሴቶችንና የህፃናትን ጤና የሚጎዱ ጎጂ ድርጊቶችን ለማስወገድ የህብረተሰብ ንቅናቄ መፍጠር፡፡

2.4 በሴቶች ላይ አካላዊና ስነ አዕምሮአዊ ችግሮችን የሚያስከትሉ ጎጂ ልምዶችንና ድርጊቶችን ለማስቀረት በሚደረገው እንቅስቃሴ ሴቶች ግንባር ቀደም እንዲሆኑ መስራት ፡፡

2.5 ሴቶች ለኤች አይቪ ኤድስና ሌሎች ተላላፊ በሽታዎች ነፃ የምርመራ አገልግሎት የሚያገኙበት እንዲሁም ከእናት ወደ ልጅ ኤች አይቪ ኤድስ እንዳይተላለፍ መድሃኒት/ አገልግሎት ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ እንዲስፋፋ መስራት፡፡

## 3. ሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች

3.1. በየደረጃው የሚገኙ ሴቶች የንባብ ባህላቸውን ለማሳደግ እንዲያስችል የቤተ መፅሃፍት አገልግሎት እንዲስፋፋ መታገል፡፡

3.2. ሴቶች በተለያዩ ክልላዊና አገራዊ በዓላት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ መታገል፡፡

3.3. የተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ለሴቶች ልዩ ትኩረት ሰጥተው ትምህርታዊና አዝናኝ ፕሮግራሞችን በሴቶች ተሳትፎ እንዲያቀርቡ መስራት፡፡

3.4. ሴቶች በወቅታዊ ሃገራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ላይ የሚመክሩበትና የተማላ ግንዛቤ የሚፈጥሩበት የተለያዩ መድረኮች እንዲኖሩ መስራት፡፡

3.5. ሴቶች ለህብረተሰቡ ነፃ ማህበራዊ አገልግሎቶችን የመስጠት ባህል እንዲያዳብሩ በተለያዩ የማህበረሰብ ነፃ አገልግሎቶች እንዲሳተፉ ማድረግ፡፡

3.6. ሴቶች ኃላቀርና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በመለየት የማስወገድና ጠቃሚ ባህሎችን በማዳበር እንዲቀጥሉ እና ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፉ መታገል፡፡

3.7. አሁን ያለውን ኃላቀርና ያልዳበረ የስራ ባህላችንን ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲሸጋገርና በሴቶች ላይ ያለውን የተሳሳተ አመለካከት እንዲቀየር መታገል፡፡

3.8.ሴቶች በአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ በመሳተፍ አካባቢያቸውን አረንጓዴ እንዲያለብሱ የተለያዩ መርሃ ግብሮችን ማዘጋጀትና በስራ ላይ ማዋል፡፡

3.9. አካል ጉዳተኛ ሴቶች ከተረጂነት ራሳቸውን እንዲላቀቁና ህብረተሰቡ በአካል ጉዳተኞች ላይ ያለው አመለካከት እዲቀየርና ራሳቸውን እንዲችሉ መታገል፡፡

# VI. የውጭ ግንኙነት መርሃ ግብር

## 1. የኢህአዴግ የሴቶች ሊግ  የውጭ ግንኙነት ዓላማ

የኢህአዴግ የወጭ ግንኙነት መርህ-ግብር መነሻ በማድረግ ከሌሎች ተመሳሳይ አደረጃጀቶች ጋር ምቹ የሆነ የስራ ግንኙነት ለመፍጠር የሚያስችልና ይህንኑ የሚያሳካ የሚከተለውን የውጭ ግንኙነት መርሃ ግብር ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

1.1. በየደረጃው የሚመሰረተው የሊግ አመራር ከኢህአዴግ አመራር ጋር በቅርበት የሚሰራ እና የድርጅቱን ውሳኔዎች የሚያከብር፣ ከሊጉ ጋር በሚጣጣም መልኩ በስራ ላይ የሚያውል እና አጠቃላይ አቅጣጫውን ከፖለቲካ ድርጅቱ የሚያገኝ ይሆናል፡፡

1.2. ሊጉ ከማህበራት ጋር እንደ አደረጃጀት የአቻነትና የመተባበር ግንኙነት የሚኖራቸዋል፡፡

1.3. ሊጉ በየደረጃው ከአሉት ማህበራት ጋር በመተባበር በጋራ ጉዳዮች ዙሪያ የመስራቱ ሁኔታ እንዳለ ሆኖ ከሌሎች ሀገሮች ሊጎች ጋርም በሀገሪቱ የውጪ ፖሊስ ፡እና የኢህአዴግ የወጭ ገንኙነት መርህ ላይ በመመርኮዝ ግንኙነት የማድረግና ወንድማማችነትን የማጠናከር፣ የመደጋገፍ፣ ልምድ የመለዋወጥ፣ ተግባራትን ሊያከናውን ይችላል፡፡

**የ2001 ዓ/ም**